# 2011 General Relief Society Meeting
## September 24, 2011

ሴትና ወንድ የልጅ ልጆቼ ስለ ሴቶች መረዳጃ ማህብር ምን እንዲያውቁ ተስፋ ያለኝ

በጁሊ ቤክ

የሴቶች መረዳጃ ማህበር ፕሬዘደንት

በእዚህ ታሪካዊ ስብሰባ ከእናንተ ጋር መነጋገር ታላቅ እድል ነው። ከእናንተ ጋር ለመሆን መቻላችንም የምንባረክበት ነው። እንደ ሴቶች መረዳጃ ማህበር ፕሬዘደንት በማገለግልበት ጊዜ፣ ለዚህች ቤተክርስቲያን የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች ጥልቅ የሆነ ፍቅር ኖሮኛል፣ እናም ጌታ ስለእኛ ምን ስሜታ እንዳለውእና ምን እንደሚጠብቅብን እይታዬን አሳድጎታል።

ይህን ንግግር “የልጅ ልጄ ስለ ሴቶች መረዳጃ ማህብር ምን እንደምታውቅ ተስፋ ያለኝ” የሚል ርዕስ ሰጥቼዋለሁ። ታላቆቼ የልጅ ልጆቼ በግለሰብ እድገት ላይ እና የጻድቅ ሴትነት ጸባይ እና ልምድን ለማሳደግ በሀይል እየሰሩ ናቸው።

በእዚህ መልእክት የምለውእነርሱን እና ይህን የሚያዳምጡትንና የሚያነቡትን የሴቶች መረዳጃ ማህበር ሲደራጅ ጌታ ለሴት ልጆቹ ምን እያሰበ እንደነበረ ግልጽ እውቀት እንዲያገኙ ተስፋ አለኝ።

**የጥንት ደቀመዛሙርትነት ንድፍ**

ሴቶቹ የልጅ ልጆቼ የሴቶች መረዳጃ ማህበር የተደራጀውበጥንቱ ቤተክርስቲያን ዘመንበነበረውየደቀመዛሙርትነት ንድፍ መሰረት እንደነበረ እንዲገባቸውተስፋ አለኝ። ጌታ ቤተክርስቲያኑን በአዲስ ኪዳን ዘመን ሲያደራጅ፣ “በአገልግሎቱ ሴቶች አስፈላጊ ተሳታፊዎች ነበሩ።” በልብ ተከታዮቹ የነበሩትን ማርታንና ማርያምን በማርታ ቤት ጎበኘ። በጊዜአቸውባህል መሰረት ማርታ ስታዳምጠውና ስታገለግለው፣ ከዚህም በላይ ለማድረግ እንደምትችል አሳያት። ማርታንና ማርያምን ሊወሰድባቸው ከማይቻለው ጥሩ ክፍል ለመምረጥ እንደሚችሉ እንዲገባቸውአደረገ። ይህ ረጋ ያለ ምክር በጌታ አገልግሎት ለመሳተፍ የተጋበዙበት ነበር። በኋላም በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ ማርታ ስለአዳኝ መለኮታዊነት ያላት ጠንካራ ምስክር ስለእምነቷ እና ስለደቀመዛሙርትነቷ አስተያየት ሰጥቶናል።

በአዲስ ኪዳን በተጨማሪ ስናነብ፣ ሀዋሪያቱ ቤተክርስቲያኗን መመስረት እንደቀጠሉ እንማራለን። ደቀመዛሙርትነት ለቤተክርስቲያኗ እድገት ተጨማሪ ስለሆኑት ታማኝ ሴቶችም ተምረናል። ጳውሎስም በኤፌሶን እና በፊልጵስዮስ ቦታዎች ስለነበሩ ሴቶች ደቀመዛሙርት ተናግሮ ነበር። ነገር ግን የጌታ ቤተክርስቲያን በክህደት ሲጠፋ፣ ይህ የደቀመዛሙርትነት ንድፍም ጠፍቶ ነበር።

ጌታ በነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ ቤተክርስቲያኑን በዳግም ለመመለስ ሲጀምር፣ በደቀመዛሙርት ንድፍ ሴቶችን እንደገና ተሳታፊ አደረጋቸው። ቤተክርስቲያኑ ከተደራጀች ከጥቂት ወሮች በኋላ፣ ጌታ ኤማ ስሚዝ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እንደ መሪና አስተማሪ እንድትሾም እና ለባለቤቷ ለነቢዩ ረጂ እንድትሆን ጌታ ራዕይ ሰጠ። ጌታን መንግስቱን ለመገንባት እንድትረዳ በተጠራችበት ጥሪ፣ እምነቷንና የግል ጻድቅነቷን እንዴት እንደምትጨምር፣ ቤተሰቧንና ቤቷን እንዴት እንደምታጠናክር፣ እና ሌሎችን እንዴት እንደምታገለግል መመሪያዎች ተሰጥተዋት ነበር።

በዚህ ዘመን ወንጌሉ በዳግም መመለስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ፣ ጌታ ታማኝ ሴቶች እንደ ደቀመዛመርቱ እንዲሳተፉ እንደሚፈልግ ሴቶቹ የልጅ ልጆቹ እንዲገባቸው ተስፋዬ ነው።

አስደናቂ ከሆኑት ስራዎቻቸው አንዱ የሚስዮን ስራ ነበር። የድሮው ቤተክርስቲያን ታላቅ እድገት የሚቻል የሆነው፣ ወንጌሉን ለማስተማር ታማኝ ወንዶች ቤተሰቦቻቸውን ትተው ወደማይታወቅ ቦታ ለመጓዝ እና ለመቸገር ፈቃደኛ በመሆናቸው ነበር። ነገር ግን እነዚህ ወንዶች በህይወታቸው ውስጥ ከነበሩት፣ ቤቶችንና ንግዶችን ከሚደፉ፣ እናም ለቤተሰቦቻቸውና ለሚስዮኖቻቸው ገንዘብ ከሚያገኙት ሴቶች ሙሉ እምነት እና ሽርክና በስተቀር ሚስዮናቸው የማይቻል እንደሆነ ያውቁ ነበር። እህቶችም በመንደራቸው የተሰበሰቡትን ብዙ ሺህ ተቀያሪዎችንም ይንከባከቡ ነበር። በአዲስ ህይወታቸው፣ እንዲሁም የጌታን መንግስት ለመገንባትና በደህንነት ስራው ለመሳተፍ፣ ጥልቅ ውሳኔ አድርገውም ነበር።

## ከክህነት ስልጣን ጋር ግንኙነት ማድረግ

ጌታ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝን የቤተክርስቲያኗን የሴቶች ድርጅት “በክህነት ስልጣን ንድፍ እክህነት ስልጣን ስር” እንዲያደራጅ፣ እና “እንዴት የክህነት ስልጣን መብቶችን፣ በረከቶችን፣ እና ስጦታዎችን ለማግኘት እንደሚችሉ” እንዲያስተምራቸው እንደተነሳሳ ሴቶቹ የልጅ ልጆቹ እንዲገባቸው ተስፋ አለኝ።

የሴቶች መረዳጃ ማህበር ስትደራጅ፣ ኤማ ስሚዝ እንደ መሪ ጥሪዋን ቀጠለች። አበረው ከሚያገለግሉት ሁለት አማካሪዎች ጋር እንደ ድርጅቱ ፕሬዘደንት ተሾመች። በታዋቂነት ምርጫ ሳይሆን፣ ይህ ቀዳሚ አመራር የተመረጠት በራዕይ፣ በሚያገለግሏቸው የተደገፉ፣ እና በክህነት ባለስልጣኖች ለጥሪአቸው የተለያዩ ነበሩ፣ በዚህም “በእግዚአብሔር፣ በራዕይ፣ እና በስልጣን ባላቸው እጅ በመጫን የተጠሩ” ናቸው። በክህነት ስልጣን ስር መደራጀት አመራሩ ከጌታ እና ከነቢያቱ ስለስራዎች ቀጥተኛ መመሪያ ለመቀበል ያስችላቸዋል። እናም የሴቶች መረዳጃ ማህበር ድርጅት የጌታ ችሎታ፣ ሰዓት፣ እና ሁኔታ ጎተራ በጥበብ እና በስርዓት ለመተዳደር እንዲችል ያደርጋል።

የመጀምሪያዎቹ ሴቶች የማስተማር፣ የማነሳሳት፣ እና እህቶችን በጌታ ደህንነት ስራ እንደሚረዱ ደቀመዛመርቶች የማደራጀት ስልጣን እንደተሰጣቸው ገብቷቸው ነበር። በእህቶች የመጀምሪያ ስብሰባዎች፣ እምነትና የግል ጻድቅን መጨምር፣ ቤተሰቦችንና ቤቶችን ማጠናከር፣ እናም እርዳታ የሚፈልጉትን ማግኘትና መርዳት እምነትን እና እህቶች የሴቶች መረዳጃ ማህበር መመሪያ አላማን ተምረው ነበር።

የሴቶች መረዳጃ ማህበር ድርጅት ቅዱሳንን በቤተመቅደስ ውስጥ ብቻ የሚገኙትን መብቶች፣ በረከቶች፣ እና ስጦታዎች ለመቀበል ለማዘጋጀት አስፈላጊው ክፍል እንደሆነ ሴቶቹ የልጅ ልጆቹ እንዲገባቸው ተስፋዬ ነው። ፕሬዘደንት ጆሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ እንዳስተማሩት፣ የሴቶች መረዳጃ ማህበር “በምድር ላይ የሚገኘው የእግዚአብሔር መንግስት ዋና ክፍል ናት” እናም “ይህችም ታማኝ አባላቷን በአባታችን መንግስት ዘለአለማዊ ህይወትን ለማግኘት እንዲችሉ የምትረዳ ነች።” ነቢዩ “ከአለም ክፋቶች ሁሉ የተለየ፣ የተመረጠ፣ ምግባረ ጥሩ፣ እና ቅዱስ የሆነ ምርጥ ማህበር መኖር ይገባዋል” ብሎ ባስተማረበት በጆሴፍ ስሚዝ ሱቅ ውስጥ በነበረው የመጀመሪያው የሴቶች መረዳጃ

ማህበር ስብሰባ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩት እህቶች ምን ስሜታ እንደነበራቸው ለመገመት ብቻ ነው የምንችለው።

የቤተመቅደስ በረከቶች የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ሴቶች ታላቅ ሽልማቶች እና ታላቅ አላማ እንደሆነ እሚያምኑት የመጀመሪያው የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች ቤተመቅደስን ታላቅ ዋጋ እንደሚሰጡት ሴቶቹ የልጅ ልጆቼ እንዲሰጡት ተስፋዬ ነው። እንደ ድሮ የሰኢቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች፣ ሴቶቹ የልጅ ልጆቼ በየቀኑ የቤተመቅደስ ቃል ኪዳኖችን ለመግባትና ለመጠበቅ ጎልማሳ ለመሆን እንዲጥሩ፣ እና ወደ ቤተመቅደስ ሲሄዱ በሀይል እንዲታጠቁና “የእግዚአብሔር እውቀት ቁልፎችን” ለመቀበል እንዲባረኩ ተስፋዬ ነው። በቤተመቅደስ ውስጥ ብቻ በሚገኙት ክህነት ስልጣን ስነስርዓቶች፣ መለኮታዊና ዘለአለማዊ ሀላፊነታቸውን ለማሟላት ይባረካሉ፣ እናም እንደ ደቀመዛመርት ለመኖር ቃል ይገባሉ። የሴቶች መረዳጃ ማህበር ያደራጀበት የጌታ አንዱ አላማ ሴቶች እርስ በራስ “በቤተእቅደስ ስነስርዓቶችና ቃል ኪዳኖች ውስጥ ለሚገኘው ለክህነት ስልጣኑ ታላቅ በረከት” እንዲዘጋጁ እንዲረዳዱበት በመሆኑ ምስጋና ይሰማኛል።

## የአለምአቀፍ እህትነት መሸሸጊያና ተፅዕኖ

የሴቶች መረዳጃ ማህበር እንደ ታላቅ አለምአቀፍ እህትነት ተፅዕኖ እና ችሎታ አስፈላጊነት ማስተዋል እንዲችሉ ተስፋ አለኝ። ከ 1842 ዓ.ም. በኋላ ቤተክርስቲያኗ ከናቩ አልፋ ተስፋፍታ ነበር፣ እናም የሴቶች መረዳጃ ማህበር ከ 170 ሀገሮች በላይ ውስጥ ትገኛለህ፣ እናም በዚህም ውስጥ እህቶች ከ 80 አመት በላይ ቋንቋዎች ይናገራሉ። በየሳምንቱ አዲስ ዎርዶችና ቅርንጫፎች ይደራጃሉ፣ እናም አዲስ የሴቶች መረዳጃ ማህበሮች በመቀጠል በሚያድገው እህትነት ተሳታፊ በመሆን “በክፍለ አህጉሮች ውስጥ ይስፋፋሉ።” የሴቶች መረዳጃ ማህበር በቁጥር ትንሽ በሆነችበትና በዩታ ብቻ በተደራጀችበት ጊዜ፣ መሮዎቿ በድርጅቱና በአካባቢው ህብረተሰባዊ ፕሮግራሞችና በእርዳታ ስራዎች ላይ ያተኩሩ ነበር። የቤት ፋክትሪዎችን ሰሩ እናም ሆስፒታሎችን ጎተራዎችን ሰሩ። እነዚያ የሴቶች መረዳጃ ማህበር ጥረቶች አሁንም በአለም ላይ ተከታይነት ያሏቸውን የደቅመዛመርትነት ንድፎችን መሰረቱ። ቤተክርስቲያኑ ስታድግም፣ የሴቶች መረዳጃ ማህበር በእያንዳንዱ ዎርድና ቅርንጫፍ አላማዎቿን ለማሟላት ችላለች።

በየቀኑ፣ የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች የስጋዊ ህይወት ፈተናዎችን እና አጋጣሚዎችን ያጋኛሉ። ሴቶችና ቤተሰቦቻቸው የሚጠብቁትን ነገሮች አለማግኘት፤ የአዕምሮ፣ የሰውነትና መንፈሳዊ በሽታዎች፤ አደጋዎች፤ እናም ሞት ያጋጥማቸዋል። አንዳንድ እህቶች የእራሳቸው ቤተሰብ ስላልነበራቸው ብቸኛነት እና ተስፋ መቁረት ይኖርባቸዋል፣ ሌሎችም የቤተሰብ አባላት ባደረጉት መጥፎ ምርጫዎች ምክንያት ይሰቃያሉ። አንዳንዶች ጦርነት ወይም ርሀብ ወይም አደጋ አጋጥመዋቸዋል፣ እናም አንዳንዶች የሱስ ስቃይ፣ ስራ ማጣትን፣ እና ብቁ የሆኑ ትምህርትና ስልጣኔ ባለማግኘታቸው ችግርን እየተማሩ ናቸው። እነዚህ ሁሉ ችግሮች እምነትን ለማሳጣትና የግለሰቦችንና የቤተሰቦችን ጥንካሬ ለመቀነስ ችሎታ አላቸው። ጌታ እህቶችን በደቀመዛመርትነት ያደራጀበት አንዱ አላማ “የሰኢቶችን ደስታ እና እድገን ከሚያስወግደው ሁሉ” ከፍ ለማድረግ እርዳታ ለመስጠት ነበር። በእያንዳንዱ ዎርድ እና ቅርንጫፍ፣ ከክህነት ባለስልጣኖች ጋር እርስ በራስ ለመጠናከር እና በቤታቸው እና በህብረተሰባቸው ውስጥ ሊጠቀመብት የሚችሉትን መፍትሄ ለማግኘት ራዕይን ለመቀበልና ለመመካከር የሚፈልጉ እህቶች የሚገኙበት የሴቶች መረዳጃ ማህበር ትገኛለች።

ሴቶቹ የልጅ ልጆቹ በሴቶች መረዳጃ ማህበር በኩል ደቀመዛሙርታቸው እንደሚስፋፉ እና ጌታ እንደሰራው አይነት ስራ ከሌሎች ጋር አብረው ለመስራት እንደሚችሉ እንዲገባቸው ተስፋ አለኝ። የቤተክርስቲያኗ እህቶች እንዲሳተፉበት የሚጠየቁት ስራ ታናሽ እና ለጌታ አስፈላጊነቱ ያነሰ አለነበሩም። በታማኝነታቸው የእርሱን ተቀባይነት ይሰማቸዋል እናም በመንፈሱ ጓደኝነት ይባረካሉ።

ሴቶቹ የልጅ ልጆቹ የሴቶች መረዳጃ ማህበር የደህንነት፣ የመሸሸጊያ፣ እና የመጠበቂያ ቦታ እንደምትሁን ማወቅ ይገባቸዋል። ጊዜዎቻችን አስቸጋሪ ሲሆኑ ታማኞቹ የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች የፅዮንን ቤት ከአለም አስፈሪ ድምጾችና ከአጥፊው መጥፎ ተጽእኖ ለመጠበቅ ይረዳሉ። በሴቶች መረዳጃ ማህበር በኩልም፣ ይማራሉ እናም ይጠናከራሉ ጻድቅ ሴቶች ተጨማሪ የሰማይ አባታችንን ልጆች ለመባረክ ይችላሉ።

## የደጋፊ እና አገልጋይ ደቀመዛሙርት

ሴቶቹ የልጅ ልጆቹ የሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት የደቀመዛሙርትነታቸው ምልክትና ቃልኪዳናቸውን የሚያከብሩበት አንድ ታላቅ መንገድ እንደሆነ እንዲገባቸው ተስፋ አለኝ። ይህ የደቀመዛሙርትነታችን ክፍል የጌታን አገልግሎት አመሳሳይ ነው። በሴቶች መረዳጃ ማህበር መጀመሪያ ጊዜዎች፣ እርዳታ ለሚያስፈጋቸው ፍላጎታቸውን እንዲያመዛዝኑ እና የሚረዱበትን እንዲሰበስቡ የሚመደቡ ቡድኖች ነበሩ። አመቶች ሲያልፉም፣ የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶችና መሪዎች ቀስ በቀስ ተምረዋል እናም ሌሎችን የሚጠብቁበትን ችሎታ አሻሽለዋል። እህቶች የሚጎበኙበት፣ የሚያስተምሩበት፣ እና የሚጎበኟቸው በማይኖሩበት ጊዜ ማስታወሻ የሚተዉበት ጊዜ ነበር። እነዚህ መለማመጃዎች የመንከባከቢያን ንድፍ እንዲማሩ ረድተዋል። በሙሴ ዘመን ህዝቦች የህግጋት ዝርዝን በመጠበቅ ላይ ያተኩሩ እንደነበሩ፣ የሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶችም እርስ በራስ እንዴት ለማጠናከር እንደሚችሉ ለማወቅ በእራሳቸው ላይ ብዙ ህጎችን አሳልፈው ነበር።

ዛሬ በእህቶችና በቤተሰቦቻቸው ውስጥ ለእርዳታ እና ለማዳን ብዙ ፍላጎት እያለ፣ የሰማይ አባታችን ከፍተኛውን ጎዳና እንድንከተል እና ደቀመዛሙርትነታችንን ልጆቹን በደንብ በመንከባከብ እንድናሳይ ይፈልግብናል። ይህ አስፈላጊ አላማ እየታሰበበት፣ መሪዎች ስለእህቶችና ቤተሰቦቻቸው መንፈሳዊና ጊዜአዊ ደህንነት እና አገልግሎት ስለመስጠት ሀተታ እንዲጠይቁ ተምረዋል። እናም የሴቶች የቤት ለቤት አስተማሪዎች “እያንዳንዷን እህት ለማወቅና ለማፍቀር፣ እምነቷን ለማጠናከር፣ እና አገልግሎት ለመስጠት”ሀላፊነት አላት።

እንደ አዳኝ ደቀመዛሙርቶች፣ እዚህ ቢኖር የሚያደርገውን ነገሮች ለማድረግ ያለንን ችሎታ እያሻሻልን ነን።፡ እርሱ የሚመለከተው ለሌሎች ማሳባችንን እንደሆነ እናውቃለን፣ እናም ስለዚህ የምናከናውናቸውን ነገሮች ዝርዝር ለመፈጸም ከመጣር በላይ እህቶቻችንን በመንከባከብ ላይ እናተኩራለን። እህቶቻችን “የሴቶች የቤት ለቤት የምትጎበኘኝ በመንፈስ እንዳድግ ረዳችኝ”እና “የምትጎበኘኝ ስለእኔ እና ስለቤተሰቤ ታስባለች”እናም “ችግር ካለኝ፣ የምትጎበኘኝ ለመጠየቅ ሳትጠብቅ መስራት እንደምትጀምር አውቃለሁ”ሲሉ፣ እንደ ሴቶች የቤት ለቤት ጎበኚዎች ውጤታማ እንደሆንን ለማወቅ እንችላለን። ለሌሎችን ማገልገል አስፈላነት የገባቸው እህቶችና መሪዎች እንዴት የሴቶች የቤት ለቤት ጉበኚዎችን ለማስተማር እና እንዴት አገልግሎታቸውን ለማቀድና ለማከናወን እንደሚችሉ ለማወቅ ይመካከራሉ።

በተጨማሪም፣ የሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት ኤጲስ ቆጶሱ መንጋዎቹን ለመንከባከብ ካለው ሀላፊነት አንዱ ክፍል ነው። ኤጲስ ቆጶስ እና የሴቶች መረዳጃ ማህበር አመራር ሀላፊነቶቻቸውን ለማሟላት የሚረዷቸው የተነሳሱ የሴቶች የቤት ለቤት ጎበኚዎች አገልግሎት ያስፈልጋቸዋል። በሴቶች የቤት ለቤት ጎበኚዎች አገልግሎት በኩል፣ የሴቶች መረዳጃ ማህበር ፕሬዘደንት የእያንዳንዷ እህት ደህንነትን ለማወቅ ትችላለች እናም ሁኔታቸውን ኤጲስ ቆጶሱን ስትጎበኝ ሀተታ ለማቅረብ ትችላለች።

ፕሬዘደትንት ሞንሰን እንዳስተማሩት፣ “የተመደብንበትን ሀላፊነት ለማሟላት ያለመነቃነቅ በእምነት ስንጥር፣ ሀላፊነታችንን ለማከናወን ሁሉንም የሚችለው እንዲያነሳሳን ስንፈልግ፣ ታዕምራትን ለማግኘት እንችላለን።” ሴቶቹ የልጅ ልጆቼ የሴቶች የቤት ለቤት ጉብኝት ጌታ እንደገና ሲመጣ እንደሚያውቀው የደቀመዛመርትነት ንድፍ እንዲሆን ሲጥሩ በዚህ ታዕምራት እንዲሳተፉ ተስፋ አለኝ።

**የሴቶች መረዳጃ ማህበር አላማን ማሟላት**

እነዚህ እና ሌሎች አስፈላጊ የሴቶች መረዳጃ ማህበር ትምህርቶች ለሴቶች የልጅ ልጆቼ Daughters in My Kingdom: The History and Work of Relief Society በሚለ መፅሀፍ ውስጥ ይገኛሉ። ይህ መፅሐፍ የሴቶች መረዳጃ ማህበርና የዚህች ቤተክርስቲያኗ ሴቶች ታሪኮችን የያዘ ነው። የአለምአቀፍ እህትነትን ከሴቶች መረዳጃ ማህበር አላማዎችና ከደቀመዛመርትነት ንድፎችና ችሎታዎች ጋር አንድ ያደርጋል። ይህም በሰማይ አባታች የደስታ አላማ ውስጥ የሴቶች ስራ አስፈላጊነትን ይመሰክራል፣ እናም የምናምንበትን፣ የምናደርገውን፣ እና የምንከራከረውን የሚያሳይ የማይነቃነቅ አርማ ይሰጣል። ቀዳሚ አመራር “ይህን መፅሐፍ እንድናጠና እና ጊዜ የለሽ የሆኑትን እውነቶችን እና የሚያነሳሱ ምሳሌዎች ህይወቶቻችን ላይ ተፅዕኖ እንዲኖረው” አበረታትተውናል።

የሴቶች መረዳጃ ማህበር ድርጅት በመለኮት የተደራጀ እንደሆነ በማወቅ፣ ፕሬዘደንት አሴፍ ኤፍ ስሚዝ ለሴቶች መረዳጃ ማህበር እህቶች እንዲህ ብለዋል፥ “አለምን መምራት፣ እንዲሁን የአለም ሴቶችን መምራት የእናንተ ሀላፊነት ነው። ...እናንተ ራስ እንጂ ጭራ አይደላችሁም።” የጌታ በዳግም መመለሻ ሲቀርብ፣ ሴቶቹ የልጅ ልጆቼ የሴቶች መረዳጃ ማህበር መሰረታዊ መመሪያዎችን እና ንድፎችን በህይወታቸው የሚከተሉ ጠንካራ፣ ታማኝ ሴቶች እንዲሆኑ ተስፋ አለኝ። የሰቶች መረዳጃ ማህበር የሚኖርበት መንገድ ሲሆን፣ በአንድነት ከሌሎች ጋር መለኮታዊ አላማ ለማሟላት ያገለግላሉ። ዳግም ስለተመለሰችው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ምስክር አለኝ፣ እናም ጌታ ነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝን የሴቶች መረዳጃ ማህበርን እንዲያደራጅ በማነሳሳቱ በዳግም ለተመለሰው የደቀመዛመርትነት ንድፍ ምስጋና አለኝ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ አሜን።